# ሚኔሶታ ለትምህርት ዓመቱ የወጣቶች ምርመራ ዘመቻ ተግባራዊ አድርጓል፡ በጽሁፍ

[አዝናኝ ሙዚቃ]

[የስክሪን ላይ ጽሁፍ] ተማሪዎች በቋሚነት የ COVID-19 ምርመራ ማድረግን በተመለከተ ምን እንደሚሉ።

[ሴት ተማሪ 1] በዚህ የፀደይ ወቅት ለምርቃት ለመብቃት ምርመራ ማድረግ ለእኔ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

[ሴት ተማሪ 2] ለስፖርት ውድድሬ በውድድሩ ላይ መሳተፍና መወዳደር እንድችል አስፈላጊ ነው።

[ወንድ ተማሪ 1] ለመመረቂያ አመት የሙዚቃና ግጥም የመድረክ ላይ ስራዬና ለመመረቅ አስፈላጊ ነው።

[የስክሪን ላይ ጽሁፍ] የሚኔሶታ የጤና መምሪያ ህጻናትና ቤተሰቦቻቸው በየ ሁለት ሳምንታቱ ውስጥ ምርመራ እንዲያደርጉ ይመክራል። በየትኛውም ከትምህርት ተጨማሪ ተግባሮች ወይም የስፖርት ተግባሮች ላይ የሚሳተፉ ህጻናት በየሳንቱ ምርመራ ማድረግ አለባቸው፡፡

[የአኖካ ዋና የትምህርት ተቆጣጣሪ፣ David Law] ይህ ተማሪዎች የበሽታውን ምልክት በማያሳዩበት ሁኔታ ምርመራ የማድረጊያ ፕሮግራም ጥቂት መቶኛ የምርመራ ውጤታቸው ፖዘቲቭ የሆኑ ተማሪዎችን የምናገኝበትን እድል በማሳደግ ከባድ ከትምህርት ተጨማሪ ተግባር ወይም የትምህርት ቀን መስተጓጎልን ለማስቀረት ያስችለናል።

[የስክሪን ላይ ጽሁፍ] ምርመራውን ማድረግ ምንም ወጪ የማያስወጣዎ ከመሆኑም በተጨማሪ በተመሳሳይ ጊዜ ለሙሉ ቤተሰብዎ ቀጠሮ ማስያዝ ይችላሉ።

[ሴት ተማሪ 1] ወደ Amory በምመጣበት ወቅት ለማህበረሰቡ የበሽታው አስተላላፊ መሆን አልፈልግም፤ በነጻ ምርመራ ማድረጉ ለኔ ቀላል ከመሆኑም በተጨማሪ ደህንነቴ መጠበቁንም ሆነ የጓደኞቼ ደህንነት መጠበቁን ለማረጋገጥ ያስችለኛል።

[ወንድ ተማሪ 2] በድጋሚ በአካል ለመገናኘት የምንፈልግ እንደመሆኑ እዚህ ነጥብ ላይ ለመድረስ በጋራ መስራት ይኖርብናል።

[የስክሪን ላይ ጽሁፍ] እንደ የፊት ጭምብል መልበስና ምርመራ ማድረግ የመሰሉ ቅድመ ጥንቃቄዎች የ COVID-19 ስርጭትን ለመቀነስ ያግዛሉ። የበለጠ መረጃ ለማግኘትና ለቤተሰብዎ የምርመራ ቀጠሮ ለማስያዝ mn.gov/covid19 ን ዛሬውኑ ይጎብኙ።

[አዝናኝ ሙዚቃ]

Minnesota Department of Health
Communications Office
PO Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
651-201-4989
health.communications@state.mn.us
www.health.state.mn.us

3/17/21 (Amharic)

*ይህን መረጃ በተለየ ፎርማት ለማግኘት በስልክ ቁጥር : 651-201-4989 ይደውሉ።*